## ደብረ ማርቆስ ጀግኖችን የማትረሳ ከተማ

ጌታ በለጠ ደበበ ( ደብር ማርቆስ)







በከተማ ያሉ መሰረተ ልማቶች ታሪክ ሰርተው ባለፉ የሀገር ባለውለታዎች ሥም ሲሰዬሙ ታሪክ የነገ ትውልድ ታሪኩን ያውቅ ዘንድ ያግዛል፡፡ የእኔዋ ደብረ ማርቆስ ለሐገር ውለታ የዋሉ ድንቅ ጀግኖችን መዘከር ተችልበታለች፡፡ከተማዋ ውስጥ ብዙ የሐገር ባለውለታች በሥማቻው ሐውልት ቆሟል፣ ትምህርት ቤት እና ከተማ ተሰይሟል፡፡

ባሻዬ! ተከተለኝ ትቂቶችን ላስተዋውቅህ፡፡

የመጀመሪያው በሥማቸው ሐውልት የቆመላቸው ታላቁ የሥነ ፅሑፍ አድባር ሐዲስ አለማዬሁ ናቸው፡፡ሐዲስ አለማዬሁ በፍቅር እስከ መቃብር ልብ ወለድ ብቻ ሳይሆን የሚታወቁት ራሳቸውም ለፍቅር እስከ መቃብር የታመኑ ብርቱ ደራሲ ናቸው፡፡ ሚስታቸው ወይዘሮ ክበበ ፀሐይ ገና በወጣትነት ዕደሜ ከሞቱባቸው በኋላ “ፍቅር ከአንች ወዲያ” በማለት ከአርባ ዓመታት በላይ በብቸኝነት ኖረዋል፡፡እኒህ የብዐር አርበኛ ከድርሰቱ በተጨማሪ በጣሊያን ወረራ ወቅት የጎጃም አርበኞችን በመያዝ ለእናት ሐገራቸው ከጠላት ጋር በብርቱ ተዋግተዋል፡፡በአምባሳደርነትም ሰርተዋል፡፡ታዲያ እኒህ ሁለገብ ጀግና በደብረ

ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የገንዘብ ድጋፍ በከተማው መሐል የክብር ሐውልታቸው "ጅንን" ብሎ ማዬት ለአይን ይማርካል፡፡

የጎጃሙ ገዥ ንግሥ ተክለሃይማኖት (አዳል ተሰማ በልጅነት ሥማቸው) ከሀገረ ገዥነታቸው በተጨማሪ በአድዋ ጦርነት ወቅት የሰሩት ጀብዱ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ዛሬ በነፃነት (በሀገር ውስጥ ያሉ ታናናሾች በሕዝባችን ላይ የሚያደርሱት በደል ሳይዘነጋ) እንኖር ዘንድ፣ ኢተዮጵያ የምትባል ሐገር ሥሟ ከአለም መዝገብ ላይ በሰፊው ይሰፍር ዘንድ የጎጃሙ ገዥ ንጉሥ ተክለሃይማኖት የዋሉት ውለታ የሚዘነጋ አይሆንም፡፡ የጀግኖችን ታሪክ በወጉ መመዝገብ የምታውቀው ደብረ ማርቆስ በከተማው ቀደምት የሆነውን ትምህርት ቤት "ንጉሥ ተክለሃይማት ትምህርት ቤት" በማለት ሰይማለች፡፡ ትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡

ምን ይኼ ብቻ ጃል! የከተማይቱ ደምቀት የሆነው የንጉሥ ተክለሃይማኖት አደባባይ የተሰዬመው በታላቁ የጎጃም ገዥ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሥም ነው፡፡ በወጋችን ላይ ይኼንን አደባባይ ያሰሩት በ1950ዎቹ የጎጃም ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ፀሐዩ እንቁሥላሴ ናቸው፡፡አንድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ደብረ ማርቆስ ላይ በንጉሥ ተክለሃይማኖት ሥም ተሰይሞ "የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነጉሥ ተክለሃይማኖት ቅርንጫፍ" በሚል አገልግሎት አየሰጠ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያን የመጀመሪያውን የሕዝብ መዝሙር የደረሱት፣ እጅግ የበዙ የቲአትር ሥራዎችን ለሐገራችን ያበረከቱ፣ ገና በልጅ ዕድሜያቸው "የቀኝጌታነት" ማዕረግ ያገኙት፣ በጣሊያን ወረራ ወቅት ብርቱ የአርበኝነት ሥራ የሰሩት የቅኔው ጌታ ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉስ ለሀገራችን ዘመናዊ ኪነ ጥበብ ዕድገት ፈር ቀዳጅ መሆናቸው በታሪክ ተመዝግቧል፡፡ ታዲያ እኒህ ጀግና ደብረ ማርቆስ መሐል ከተማ ላይ በሥማቸው አንድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ተሰይሞላቸዋል፡፡የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቀኝጌታ ዮፍታሔ ንጉሴ ቅርንጫፍ ይላል፡፡ እውነት ለመናገር ከዚህ የንግድ ባንክ የገዛ ንብረቴ የሆነውን ብር ሳወጣ ክበር ይሰማኛል፡፡

በመጨረሻም ደብረ ማርቆስ የአሁኑን ሥሟን ከመያዟ በፊት መንቆረር በሚል ሥያሜ የመሰረቷት የጎጃሙ ገዥ ደጃዝማች ተድላ ጓሉ መሆናቸው ተደጋግሞ ተነግሯል፡፡ ታዲያ

ባለፈው ጊዜ ደብረ ማርቆስ ከተማ “ሪጅኦፖሊታን” የተሰኘውን የከተማ ማዕረግ ስታገኝ እና በክፍለ ከተሞች ስትዋቀር የአንዱ ክፍለ ከተማ የተሰየው በደብረ ማርቆስ (በያኔው መንቆረር) መስራች ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ሥም ነው፡፡ አሁን እኔ የምኖረውም በደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር በደጃዝማች ተድላ ጓሉ ክፍለ ከተማ ነው፡፡

ደብረ ማርቆስ ከተማ አሁን ልትዘክራቸው የሚገቡ ብዙ የሐገር ባለውለታች አሉ፡፡ በተደጋጋሚ ሥማቸውን እና ሥራቸውን ፅፈናል፡፡ ወደፊትም እንፅፋለን፡፡ ደራሲ፣ አርበኛ እና መምህር ተመስገን ገብሬ የመጀመሪያው ነው፡፡ ተመስገን ገብሬ ደብረ ማርቆስ ከተማ ከቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን አጠገብ ነው ተወልዶ ያደገው፡፡ ደብረ ማርቆስንም “የፀሐይ ራስ” ይላታል፡፡